

# +++ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ +++

# የዕለት እንጀራ

**የፍልሰታ ጾም - ፱ኛ ቀን [ ፪፻፳፯ኛው እንጀራ] ነሐሴ ፱ ፳፻፩**



እስከ ነሐሴ ፲፮ (Aug 21) የፍልሰታ ለማርያም ጾም ነው። ፍልሰታ ማለት ፈለሰ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማዛወር የነበሩበትን ሀገር ለቆ ወደ ሌላ ሀገር መሰደድ መፍለስ ማለት ነው ፡፡ ጾመ ፍልሰታ ሲባልም የእመቤታችን ሥጋ ከጌቴሰማኒ ወደ ገነት መፍለስን በኋላም በገነት በዕፀ ሕይወት ሥር ከነበረበት መነሣቱን ለማመልከት የሚነገር ነው ፡፡

ስለዚህም ነገር ጾምን፥ ወደ እግዚአብሔርም ለመንን: እርሱም ተለመነን።

**ዕዝራ ፰፡፳፫**

መልካም እረኛ እኔ ነኝ ፥
አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው
የራሴን በጎች አውቃለሁ
የራሴም በጎች ያውቁኛል ፤
ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ።
ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ ፤
እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል
ድምፄንም ይሰማሉ ፥
አንድም መንጋ ይሆናሉ
እረኛውም አንድ።

**ዮሐንስ ፲፡ ፲፬-፲፮**

አያሌ ቀንም አዝን ነበር በሰማይም አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር::

**ነህምያ ፩፡ ፬**

## በዚህ ቀን ከሚታሰቡት መካከል

## ጲላጦስ፣ ሊቀ ጳጳስ

### የዕለቱ ምስባክ ፡

ወትቀውም ንግሥት በየማንከ
በአልባሰ ወርቅ እጹፍት ወኅቡርት
ስሚዒ ወለትየ ወአጽምኢ እዝነኪ

መዝሙር ፵፬፡ ፲-፲፩

### ትርጉም ፡

በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና
ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች።
ልጄ ሆይ፥ ስሚ እዩ ጆሮሽንም አዘንብዩ